*ከኀቡ-ዉ.ቃው ጥቅምት 30/2000*

*ኦንታሪዮ-ካናዳ*

# “ማህተብ፤በጠስን!”

ማህተብ በጥሰ-ን

ደም-ስጋ ተረማምደ-ን

በአስከሬኑ ላይ ፤ቆመን

ከህሊናችን፤ተጣልተን

የቀበሮ ባህቱን

በጋሻው ተማምነ-ን

በጋሻውን፤ ተከልለ-ን

አዛ-በ-ትን፤ተዛ-በ-ት-ን

ስጋችን በለጠብን

አደራ ቀርጥፈን በልተን

ምቾት በዛና፤ሰባን?

እንድ ትግል ጀማሪ፤ሰራን

የትግሉ-ግለት፤አስፈራን

አዲሱ ፋሽን፤አማረን

ደዌው ተጠናወተን

“ኮሌክቲቭ!፤ሴሌክቲቭ!”

“ዲሞክራሲ!፤ትራንስፓረንሲ!”

አርቲ-ቡርቲ ጠቃቅሰ-ን

አምባገነን፤ምንትስ ብለ-ን

በአገር ላይ፤አኮረፍን

ስንቱን ቤተስብ አሳዘንን

በስንቱ ተስፋ ቀለድን

ቁልቁል፤ሰለጠንን

ባልንጀራችንን፤ከደን

ከጀርባው ተዋውለን

በቁም ቅዠት ታፍነን

እግር የሌለው፤ምናብ-መንበን

ወያኔን አግዝፈን አይተን

ቀለጥን፤በቁም ሸናን

ልንወይን፤ተዳፋን

ያለቤታችን፤አድረን

በሰው ጎጆ ጎምዥተን

በ እራሳችን፤ቀናን

አዲስ-ልክፍት፤አቀነቀን

ማህተባችንን፤በጠስን

ወደ ሲኦል አቀናን

እትፍ-ድርብ፤መኮነን።

“ወ-መለስ-በረከት. . .

ዓዚም፤የጣሉብን

ተስቦው ደረሰን!

በ ዕቁብ ላይ ዕቁብ

በ ዕድር ላይ ዕድር

በ ገብርኤል ላይ ገብርኤል

በ ሲኖዶስ ላይ ሲኖዶስ

በ ቅንጅት ላይ ቂል-ቀንጃት

በ ኢሕአፓ ላይ ኢ-ኢሕአፓ

በ ሬዲዮ ላይ ሬዲዮ

በ ዲሞክራሲያ ላይ ደቦ-ክራሲያ

በ ቅፅ 33 ላይ ሰላሳ ሶስት

የ እብደት፤ጡዘት

ዘመነኛ ሱረት

በጆሮ ደግፍ ላይ ዕንቅርት

ዝቅጠት፤ሁለት

“ስልጠና” ሁለት

ደሞ እንደ ድርጅት!

አልሆነም እንጂ ቢሆንማ

በ ገልም ሆነ በጀማ

በ ኢትዮጵያዬ በ እማማ

ከሃዲ ባገር ላይ ሲስማማ

ሲዋዋል አገር ሊያስቀማ

ሕዝብ አሳስሮ ሲያደማ

ከነጫጭባ አድሮ ሲ-ያ-ማ

“የድርጅት ውስጥ ጉዳይ ነው”

ዝም ብለህ ነው ማየት

የሚሉት የቀን ቅዠት

ወዴት? ወዴት?፤ለመጠጋት

የምን ሰበብ፤የምን ቅጥፈት

ለኔ ባንዳ የለው ልዩነት

ከሃዲ-ሁላ፤ሸለፈት

## አቐራጭ የለው ነፃነት

ዕውነቱን ተናግሮ፤. . .

. . .ማደር የመሸበት

ነው እንጂ የዠግና ኩራት

እጅ ሰጥቶ፤ነ-ፃ-ነ-ት?

አቤት! ውርደት፤አቤት ቅሌት!

**የ እኛስ ጌጥ እምቢኝ ናት!**

**የ አባት ዕዳ የወረስናት**

**እ-ን-በ-ል--አ-ስ-ራ-ሁ-ለ-ት**

**ከዚህ በታች ያለውን ለህዳጣኑ ቆም ብለው እንዲያስብ የተዋስኩት ነው**

“እሳት አንሆን አበባ፤በ ዕቅ-ዕንቅ ስንባባ

ባከነች ልጅነታችን፤እየቃተትን ስናነባ

ፈራን!

ህብረት ፈራን፤ፍቅር ፈራን!

የነፍስን አንደበት ዘጋን

ፈራን!

ልጅነት የለገሰንን፤የፍቅር አምላክ በጥበቡ

በረቂቂ ያለበሰንን፤በመለኮት የቀባንን

ህብረት ፈራን

ፍቅር ነሳን”

<u>ከሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህን የተወሰደ</u>

# ቸር ይግጠመን